# ትምህርት 23

1. እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ የሰጣቸው ልጅ ማን ይባል?

ሀ- ይስሐቅ።

2. አብርሃም እግዚአብሔር ከይስሐቅ ዘር አዳኝ ለማምጣት ማቀዱን ያውቅ ነበር?

ሀ- አዎን።

3. እግዚአብሔር አብርሃም ይስሐቅን እንዲሠዋለት ማዘዝ የቻለው እንዴት ነው?

ሀ- ለአብርሃም ሕይወት የሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ።

ለ- ለይስሐቅ ሕይወት የሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ።

ሐ- የሁሉም ሰዎች ጌታ እግዚአብሔር ስለሆነ።

4. እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ ይስሐቅ የብዙዎች አባት እንደሚሆንና ከዘሩም አዳኝ እንደሚመጣ ቃል ገብቶለታል። እግዚአብሔር አሳቡን ለወጠ?

ሀ- አልለወጠም።

5. አብርሃም እግዚአብሔር አሳቡን ይለውጣል ብሎ አስቦ ነበር?

ሀ- አላሰበም።

ለ- አብርሃም በእግዚአብሔርና በተስፋው ቃሉ አመነ።

6. አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ከሠዋ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል ብሎ አመነ?

ሀ- ይስሐቅን ከሠዋ እግዚአብሔር ከሞት ያስነሣዋል ብሎ አመነ።

7. አብርሃም ይስሐቅን ማዳን ያልቻለው እንዴት ነው?

ሀ- አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት ቢላዋውን አንስቶ ስለነበር ነው።

8. ይስሐቅ ራሱን ማዳን ያልቻለው እንዴት ነው?

ሀ- አብርሃም እጆቹንና እግሮቹን አሥሮት ስለነበር።

9. ሌሎች ሰዎች እኛን ማዳን ይችላሉ?

ሀ- አይችሉም።

10. እኛ ራሳችንን ማዳን እንችላለን?

ሀ- አንችልም።

11. እኛን ማዳን የሚችለው ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ብቻ ነው።

12. ለአብርሃም የተናገረውና ይስሐቅን ያዳነው ማን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

13. በይስሐቅ ምትክ የተሠዋውን መሥዋዕት ያዘጋጀው ማን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

14. እግዚአብሔር አውራውን በግ በቀንዶቹ ለምን አሠረው?

ሀ- እግዚአብሔር በይስሐቅ ምትክ የሚቀበለው ፍጹም የሆነውን መሥዋዕት ብቻ ስለሆነ ነው።

15. አብርሃም ቦታውን «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ብሎ የጠራው ለምንድን ነው?

ሀ- አብርሃም እግዚአብሔር አውራውን በግ እንዳዘጋጀ ሁሉ አንድ ቀን ሕዝቡን ለማዳን አዳኝ ያዘጋጃል ብሎ በእግዚአብሔር ስላመነ ነው።

- የአብርሃም ሚስት ሣራ ሞተች፤ ይስሐቅ በእናቱ ሞት አዘነ፣

- አብርሃም ሚስቱ ሣራ ከሞተች በኋላ፥ ልጁ ይስሐቅ እንዲጽናና ምን አደረገለት?

ዘፍጥረት 24፡67 & 25፡20

67- ይስሐቅም ርብቃን ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን ይዟት ገባ፤ አገባትም፤ ሚስት ሆነችው፤ እርሱም ወደዳት። ይስሐቅም ከእናቱ ሞት ተጽናና።

20- ይስሐቅ ርብቃን ሲያገባ ዕድሜው አርባ ዓመት ነበር። ርብቃ በሰሜን ምዕራብ ሜስጴጦሚያ የሚኖረው የሶርያዊው የባቱኤል ልጅ፥ የሶርያዊውም የላባ እኅት ነበረች።

- አብርሃም ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት አጋባው።

- የይስሐቅ ሚስት ስሟ ማን ነበር?

- ርብቃ።

- ርብቃ የተወለደችው አስቀድሞ አብርሃም እግዚአብሔር ወደ ከነዓን ምድር እንዲሄድ ሳይመራው በፊት በኖረበት አገር ነበር።

- ከጥቂት ጊዜ በኋላ አብርሃምም ደግሞ ሞተ።

- የይስሐቅ ሚስት ርብቃ መካን ስለ ነበረች ልጅ መውለድ አልቻለችም።

- ነገር ግን ይስሐቅ ስለ እርሷ ጸለየ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰማ።

ዘፍጥረት 25፡21-23

21- ይስሐቅ ርብቃ መካን ስለ ነበረች፣ ስለ እርሷ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰማ። ርብቃም ፀነሰች።

22- ልጆቹም በማኅፀኗ ውስጥ እርስ በርሳቸው ይጋፉ ጀመር፤ እርሷም፣ «ለምን እንዲህ ይሆንብኛል?» ብላ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ሄደች።

23- እግዚአብሔርም እንዲህ አላት፡- «ወገኖች በማኅፀንሽ አሉ፤ ሁለትም ሕዝቦች ከውስጥሽ ተለያይተው ይወጣሉ፤ አንደኛው ከሌላው ይበረታል። ታላቁም ለታናሹ አገልጋይ ይሆናል» አላት።

- ርብቃ ከመውለዷ በፊት ስለ ልጆቿ እግዚአብሔርን ጠየቀችው።

- እግዚአብሔር ምን መለሰላት?

- እግዚአብሔርም ርብቃ መንታ ልጆች እንደምትወልድና ታላቁም ለታናሹ እንደሚገዛ ነገራት።

- የርብቃ ልጆች ከመወለዳቸው በፊት እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሁሉንም ነገር ያውቅ ነበር።

- የርብቃ ልጆች ከመወለዳቸው በፊት እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሁሉንም ነገር እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

- እግዚአብሔር ስለ ሁሉም ሰው ሁሉንም ነገር ያውቃል።

- ከእግዚአብሔር የተሰወረ አንዳች ነገር የለም።

- እኛ ከመወለዳችን በፊት እግዚአብሔር ስለ ሁላችንም ያውቃል።

- እግዚአብሔር በእኛ ላይ ባለፈው የሆነውን ሁሉ ያውቃል።
- እግዚአብሔር በእኛ ላይ አሁን እየሆነ ያለውን ሁሉ ያውቃል።
- እግዚአብሔር በእኛ ላይ ወደፊት የሚሆነውን ሁሉ ያውቃል።

- ከጥቂት ጊዜ በኋላ ርብቃ መንታ ልጆችን ወለደች።

ዘፍጥረት 25፡24-26

24- ርብቃ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስም፥ እነሆ በማሕፀንዋ መንታ ልጆች ነበሩ።

25- በመጀመሪያ የተወለደው ቀይ፥ ሰውነቱ በሙሉ ጸጉር የለበሰ ነበር። ስለዚህ ስሙ ዔሳው ተባለ።

26- ከዚያም ወንድሙ ተወለደ፤ በእጁ የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ወጣ፤ ከዚህ የተነሣ ስሙ ያዕቆብ ተባለ።

- ርብቃ የወለደቻቸው የሁለት መንታ ወንዶች ልጆች ስም ማን ማን ይባል ነበር?

- ዔሳውና ያዕቆብ።

- ዔሳው የበኩር ልጅ ነበር።

## ዘፍጥረት 25፥27ሀ

27- ልጆቹም አደጉ። ዔሳው ጐበዝ ዐዳኝ፣ የበረሐም ሰው ሆነ።

- ዔሳው ጐበዝ አዳኝ ነበር። ብዙ ጊዜውን በዐደን ያሳልፍ ነበር።
- ዔሳው በእግዚአብሔር ያምን ነበር?
- አያምንም።

- ያዕቆብ ሁለተኛው ልጅ ነበር።

## ዘፍጥረት 25፥27ለ

27- ያዕቆብ ግን ጭምት ከድንኳኑ የማይወጣ ሰው ነበር።

- ያዕቆብ በጎችና ከብቶችን ይጠብቅ ነበር። ጭምት ሆኖ በድንኳን ውስጥ ይኖር ነበር።

- ያዕቆብ በእግዚአብሔር ያምን ነበር?
- አዎን።

- አንድ ቀን በዔሳውና በያዕቆብ መካከል አንድ ነገር ሆነ።

## ዘፍጥረት 25፥29-34

29- አንድ ቀን ያዕቆብ ወጥ እየሠራ ሳለ፣ ዔሳው እጅግ ተርቦ ከዱር መጣ።

30- ዔሳውም ያዕቆብን፣ «ቶሎ በል፤ በጣም ርቦኛልና ከዚህ ቀይ ወጥ አብላኝ» አለው። ስለዚህ ስሙ ዔዶም ተባለ።

31- ያዕቆብም፣ «በመጀመሪያ ብኩርናህን ሽጥልኝ» አለው።

32- ዔሳውም «እነሆ፣ ልሞት ደርሻለሁ፣ ታዲያ ብኩርናው ምን ያደርግልኛል!» አለ?

33- ያዕቆብም ዔሳውን፣ «እንግዲያማ፣ አስቀድመህ ማልልኝ» አለው። ስለዚህም ማለለት፤ ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠለት።

34- ያዕቆብም ለዔሳው እንጀራና የምስር ወጥ ሰጠው። እርሱም ከበላና ከጠጣ በኋላ ተነሥቶ ሄደ። ዔሳው ብኵርናውን እንዲህ አድርጎ አቃለላት።

- አንድ ቀን ዔሳው በጣም ርቦት ከዐደን ተመለሰ።

- ዔሳው ያዕቆብ ቀይ ወጥ በመሥራት ላይ መሆኑን ተመልክቶ ከወጡ እንዲሰጠው ጠየቀው?

- ዔሳው ስለ ተራበ ብኵርናውን ለያዕቆብ በጥቂት ቀይ ወጥ ሸጣት።

- ዔሳው ብኵርናውን ለምን ሸጠ?
- እንደ ትልቅ ነገር ስላልቆጠረው ነው።

- ዔሳው ትልቅ ቦታ የሰጠው ለምን ነበር?

- ዔሳው ትልቅ ቦታ የሰጠው ለሆዱ ነበር።
- ዔሳው ትልቅ ቦታ የሰጠው ለሥጋው ነው።

- ዔሳውና ያዕቆብ የሚለያዩት እንዴት ነበር?

- ዔሳው ኃጢአት ባለበት ዓለም መወለዱን አያሰብም ነበር።
- ያዕቆብ ኃጢአት ባለበት ዓለም መወለዱን ያውቅ ነበር።

- ዔሳው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንደፈጸመ አያሰብም ነበር።

- ያዕቆብ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መፈጸሙን ያውቅ ነበር።

- ዔሳው ኃጢአት ዘላለማዊ ሞት እንደሚያስከትል አያሰብም ነበር።
- ያዕቆብ ኃጢአት ዘላለማዊ ሞት እንደሚያስከትል ያስብ ነበር።

- ዔሳው እግዚአብሔርን መከተል አይፈልግም ነበር።
- ያዕቆብ እግዚአብሔርን መከተል ይፈልግ ነበር።

- ዔሳው እግዚአብሔር እርሱን ለማዳን አዳኝ እንዲልክ አይፈልግም ነበር።

- ያዕቆብ እግዚአብሔር እርሱን ለማዳን አዳኝ እንዲልክለት ይፈልግ ነበር።

- የበኩር ልጅ ስለሆነ ብኩርና የዔሳው ነበር።
- የበኩር ልጅ ስለሆነ እግዚአብሔር አዳኝ የሚልከው ከዔሳው ዘር ነበር።

- ዔሳው ግን ብኩርናውን እንደ ትልቅ ነገር አይቆጥረውም ነበር።

- ዔሳው እግዚአብሔር ከእርሱ ዘር አዳኝ እንዲልክ አልፈለገም።

- ዔሳው የፈለገው ቀይ ወጥ ብቻ ነበር።
- ዔሳው የፈለገው ሆዱ የነገረውን ብቻ ነበር።

- እኛስ ሆዳችን የነገረንን ነገር ወይስ እግዚአብሔርን ነው የምንከተለው?

- እኛስ ሥጋችን የነገረንን ነገር ወይስ እግዚአብሔርን ነው የምንከተለው?

- ሆዳችንን የምንከተል ከሆነ ወደ ሞት ይመራናል።

- ሥጋችንን የምንከተል ከሆነ ወደ ሞት ይመራናል።

- እግዚአብሔርን የምንከተል ከሆነ እርሱ ወደ ሕይወት ይመራናል።

- ዔሳው እግዚአብሔርን ስላላመነ እግዚአብሔር ያዕቆብን መረጠ።

- ዔሳው በእግዚአብሔር ስላላመነ እግዚአብሔር ከያዕቆብ ዘር አዳኝ ለመላክ ወሰነ።

- እግዚአብሔር በያዕቆብ ዘር በኩል አዳኝ ለመላክ የፈለገው ለምንድን ነው?

- ዔሳው በእግዚአብሔር ስላላመነ ነው?

- ዔሳው በእግዚአብሔር ስላላመነ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ብኩርናውን ሰጠው።

- እግዚአብሔር ለያዕቆብ ብኩርናን በመስጠቱ ዔሳው እጅግ በጣም ተናደደ።

ዘፍጥረት 27፡41

41- አባቱ ያዕቆብን ስለ መረቀው፣ ዔሳው በያዕቆብ ላይ ቂም ያዘ፤ በልቡም፣ «ግድ የለም፤ የአባቴ መሞቻው ተቃርቦአል። ከልቅሶው በኋላ ወንድሜን ያዕቆብን እገድለዋል» ብሎ አሰበ።

- ዔሳው በጣም ስለ ተናደደ ያዕቆብን ሊገድለው ዐቀደ።

- ዔሳው ያዕቆብን ለመግደል ማቀዱን የያዕቆብ እናት ርብቃ ሰማች።

- ስለዚህም ርብቃ ያዕቆብን ጠርታ እርሷ ወደ ተወለደችበት አገር እንዲሄድ ነገረችው።

ዘፍጥረት 27፡42-44

42- ርብቃ ታላቁ ልጇ ዔሳው ያሰበው በተነገራት ጊዜ፣ ታናሹን ልጇን ያዕቆብን አስጠርታ እንዲህ አለችው፤ «ወንድምህ ዔሳው ሊገድልህ ጊዜ እየጠበቀ ነው።

43- አሁንም፣ ልጄ ሆይ፤ እኔ የምልህን አድርግ፤ በካራን ምድር ወደሚኖረው ወደ ላባ ቶሎ ሽሽ።

44- የወንድምህ ቁጣ እስከሚበርድ እዚያው ቆይ፤»

- ያዕቆብ አባቱንና እናቱን ትቶ ወደ ካራን ምድር ተጓዘ።

- ካራን የያዕቆብ እናት ርብቃ የተወለደችበት ምድር ነበር።

- ካራን የያዕቆብ አያት አብርሃም እግዚአብሔር ወደ ከነዓን ሳይመራው በፊት የኖረበት አገር ነበር።

- ካራን እጅግ በጣም ሩቅ ስለ ነበር የያዕቆብ ጉዞ ብዙ ቀናትን ፈጅቶ ነበር።

- በዚያን ሌሊት ያዕቆብ እንደተኛ እግዚአብሔር ሕልም አሳየው።

ዘፍጥረት 28፡10-13ሀ

10- ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነሥቶ ወደ ካራን ሄደ።

11- ወደ አንድ ስፍራ እንደ ደረሰም፣ ፀሐይዋ ጠልቃ ስለ ነበር፣ ዐዳሩን በዚያ አደረገ፤ በአቅራቢያው ከነበሩትም ድንጋዮች አንዱን ተንተርሶ ተኛ።

12- በሕልሙም ጫፍ ሰማይ የሚደርስ መሰላል በምድር ላይ ቆሞ፣ በላዩም የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡና ሲወርዱ አየ።

13- እግዚአብሔር ከጫፉ ላይ ቆሞ ነበር።

- እግዚአብሔር በሕልም ለያዕቆብ ምን አሳየው?

- ለያዕቆብ መሰላል አሳየው።

- የመሰላሉ የታችኛው ጫፍ የት ደርሶ ነበር?
- የመሰላሉ የታችኛው ጫፍ መሬትን ነክቶ ነበር።

- የመሰላሉ የላይኛው ጫፍ የት ደርሶ ነበር?
- የመሰላሉ የላይኛው ጫፍ ሰማይን ነክቶ ነበር።

- መሰላሉ መሬትን መንካቱና እስከ ሰማይ መድረሱ ምንን ያሳያል?

- መሰላሉ መሬትንና ሰማይን በአንድነት ያገናኘ መሆኑን።

- በመሰላሉ አናት ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- በመሰላሉ ላይ ይወጡና ይወርዱ የነበሩት እነማን ነበሩ?
- መላእክት።

- መላእክት በመሰላሉ ላይ መውጣታቸውና መውረዳቸው ምንን ያሳያል?

- እግዚአብሔር የያዕቆብ አምላክ ለመሆን መፈለጉን።

- እግዚአብሔር ለያዕቆብ ይህንን ሕልም ለምን አሳየው?

- በዚህ ህልም እግዚአብሔር ያዕቆብን ስለሚመጣው አዳኝ እያስተማረው ነበር።

- እግዚአብሔር በሕልም ስለ አዳኙ ለያዕቆብ ምን እያስተማረው ነበር?

- ልክ መሰላሉ ሰማይንና ምድርን እንዳገናኘ ሁሉ እግዚአብሔር የሚልከው አዳኝ በምድር የሚኖሩትን ሰዎችንና በሰማይ የሚኖረውን እግዚአብሔርን እንደሚያገናኛቸው።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከአዳምና ከሔዋን ጋር አብሮ ነበር።

- ነገር ግን አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ ከእግዚአብሔር ተለዩ።

- አዳምና ሔዋን ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱበት ምንም መንገድ አልነበረም።

- ነገር ግን እግዚአብሔር በምድር የሚኖሩትን ሰዎችንና በሰማይ የሚኖረውን እግዚአብሔር እንደገና የሚያገናኝ አዳኝ ለመላክ ቃል ገባ።

- አዳኙ ሰዎችን ለማዳን መጣ። ከዚህ የተነሣም እግዚአብሔርና ሰው ዳግም ኅብረት ማድረግ ቻሉ።

- ይህችን ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- ፓትሪክና ዮሴፍ በጣም ጥሩ ወዳጆች ነበሩ።

- ጠላታቸው ግን ሁለቱንም ይጠላ ነበር።
- ጠላታቸው በወዳጅነታቸው ይቀና ነበር።

- አንድ ቀን ጠላት ፓትሪክንና ዮሴፍን የሚያጣላበትን መንገድ ፈለገ።

- ጠላት ወደ ፓትሪክ ሄዶ ዮሴፍ ሊጐዳው እንደሚፈልግ ነገረው።

- ፓትሪክ የጠላቱን ውሸት አምኖ ከወዳጁ ከዮሴፍ ተለየ።

- እንዲህም ሆኖ ዮሴፍ ፓትሪክን ይወድድ ስለ ነበር ወዳጅነታቸውን ለማደስ መንገድ ይፈልግ ነበር።

- ዮሴፍ ጠላት እንዳታለለው እንዲያስረዳው ልጁን ወደ ፓትሪክ ላከ።

- በልጁ ምክንያት ዮሴፍና ፓትሪክ ወዳጅነታቸውን እንደገና ቀጠሉ።

- ሰይጣን አዳምና ሔዋንን አታለለ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተለዩ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱንና ሰዎችን በድጋሚ ወደ አንድነት የሚያመጣ አዳኝ እንደሚልክ ቃል ገባ።

- መሰላሉ ወደ ሰማይ ለመድረስ ብቸኛ መንገድ እንደ ሆነ ሁሉ ወደ ሰማይ ለመድረስ ብቸኛው መንገድ አዳኙ ነው።

- በሕልም እግዚአብሔር ለያዕቆብ ተናገረ።

ዘፍጥረት 28፥13ለ-15

13- የአባትህ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ የተኛህበትን ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ።

14- ዘርህ እንደ ምድር አሸዋ ይበዛል። በምዕራብና በምሥራቅ፣ በሰሜንና በደቡብ ትስፋፋለህ፤ የምድርም ሕዝቦች ሁሉ በአንተና በዘርህ አማካይነት ይባረካሉ።

15- እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤ በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁ፤ የሰጠሁህን ተስፋ እስከፈጽምልህ ድረስ አልተውህም።

- ዛሬ እግዚአብሔር ለሰዎች በይበልጥ የሚናገረው እንዴት ነው?

- ዛሬ እግዚአብሔር ለሰዎች በይበልጥ የሚናገረው በመጽሐፉ በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ነው።

- እግዚአብሔር ለያዕቆብ የተናገረው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር ለያዕቆብ ተስፋ እየሰጠው ስለነበር።

- እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጣቸውን ተስፋዎች አሁን ደግሞ ለያዕቆብ እየሰጠው ነበር።

- እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው ተስፋ ምን ነበር?

- እግዚአብሔር ለያዕቆብ ብዙ ዘሮችን እንደሚሰጠው።

- እግዚአብሔር ያዕቆብን እንደሚባርከው።

- እግዚአብሔር ከያዕቆብ ዘሮች አንዱ የሆነውን አዳኝ ልኮ ሰዎችን ሁሉ እንደሚባርክ ቃል ገባ።

- እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ የሰጠውን ተስፋ ረስቷል?
- አልረሳም።

- እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ የሰጠውን ተስፋ አይረሳም።

- እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ የሰጠውን ተስፋ የማይረሳው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር የማይረሳ ስለሆነ።

- እግዚአብሔር ስለማይለወጥ።
- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ተስፋውን ስለሚጠብቅ።

- ሲነጋ ያዕቆብ ጉዞውን ቀጠለ።

ዘፍጥረት 29፡1

1- ያዕቆብ ጉዞውን ቀጠለ፤ የምሥራቅም ሰዎች ወደሚኖሩበት ምድር ደረሰ።

- ያዕቆብ ጉዞውን ቀጥሎ በመጨረሻም ካራን ደረሰ።
- በካራን ያዕቆብ ለብዙ ዓመታት ኖረ።

- በካራን ያዕቆብ ሁለቱን እኅትማማቾች አገባ የ12 ወንዶች ልጆች አባትም ሆነ።

- ያዕቆብ ለብዙ ዓመታት በካራን ምድር ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር በድጋሚ ያዕቆብን ተናገረው።

- በካራን ሳለ እግዚአብሔር ለያዕቆብ የተናገረው ምንድን ነው?

ዘፍጥረት 31፡13

13- «የድንጋይ ሐውልት በማቆም ዘይት ቀብተህ የተሳልህባት የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ፤ አሁንም ይህን አገር ፈጥነህ ልቀቅ፤ ወደ ተወለድህበትም ምድር ተመልሰህ ሂድ አለኝ።»

- ያዕቆብ ለብዙ ዓመታት በካራን ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግ ነገረው?

- ያዕቆብ ካራንን ለቅቆ ወደ ከነዓን ምድር እንዲመለስ ነገረው።

- ያዕቆብ ወደ ከነዓን በመመለስ ላይ ሳለ እግዚአብሔር ለያዕቆብ አዲስ ስም ሰጠው።

ዘፍጥረት 32፡28

28- እግዚአብሔርም፥ «ከእንግዲህ ስምህ እስራኤል እንጂ ያዕቆብ አይባልም» አለው።

- እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው አዲስ ስም ማን የሚል ነበር?
- እስራኤል።
- እስራኤል ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መታገል ማለት ነው።